

ሰንደቅ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር 292 ረቡዕ ሚያዝያ 5 2003

ሥነ-ሕዝብንና ጤናን ያቀናጀ የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም

ፒ ኤች ኢ ኢትዮጵያ (Population, Health and Enironment / PHE) ኮንሶርትየም የተመሠረተው ከሦስት ዓመት በፊት ነው። አላማውም የስነ-ህዝብ፣ የጤናና የአካባቢ ጉዳይ በየሴክተሩ ተበታትኖ ከሚሰራ ይልቅ ውጤታማ የሚሆነው አቀናጅቶ ሲሰራ መሆኑን ያመኑ ሰባት ድርጅቶች እንዳቋቋሙት ይነገራል። ፖፑሌሽን ሔልዝ ኢንቫይሮመንት ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም በሰባቱ ድርጅቶች ከተቋቋመ ወዲህ እጅግ በርካታ የስነ-ህዝብ፣ የጤናና የአካባቢ ጉዳዮች እና በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ከአባልና አጋር ድርጅቶች ጋር እያደረገ ያለውን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ከፒ ኤች ኢ ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም ዳይሬክተር ከአቶ ነጋሽ ተክሉ ጋር ባደረግነው ሰፊ ቆይታ ቃኝተናል። አቶ ነጋሽ ተክሉ በኢንተርናሽናል ሪሌሽን (ዓለም አቀፍ ግንኙነት) የማስተርስ ዲግሪ ባለቤት ሲሆኑ፣ በተለይም ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልን ከማቋቋም ጀምሮ ለ14 ዓመታት እንደመሩ ይታወቃል። በአሁኑ ሰዓት በጤና በስነ-ህዝብ እና በአካባቢ ጉዳዮች ዙሪያ የቅንጅት ሥራ በሚሰራው ፒ ኤች ኢ ኢትዮጵያ ኮንሰርቲየም ዳይሬክተር ሲሆኑ፣ ይህን ቃለ-መጠይቅ ለመስራት ቀጠሮ በያዝንበት ዕለት በፒ ኤች ኢ ዙሪያ ከአባልና ከአጋር ድርጅቶች ለመጡ 25 ተሳታፊዎች የአሠልጣኞች ሥልጠና በሀርመኒ ሆቴል እየሰጡ ነው ያገኘኋቸው። ሰልጣኞቹ ከመላው ሀገሪቱ የተውጣጡ እንደሆኑም ከአቶ ነጋሽ ለመረዳት ችያለሁ።

በናፍቆት ዮሴፍ

አቶ ነጋሽ ተክሉ

ሰንደቅ፡- አቶ ነጋሽ የኮንሶርቲየሙ ዳይሬክተር ነዎት። የመሰረቱትስ እርስዎ ነዎት?

አቶ ነጋሽ፡- ኮንሶርትየሙን የመሰረትኩት እኔ ነኝ አልልም። ግን በምስረታው አስተዋፅኦ አድርጌ ሊሆን ይችላል። ለምስረታው ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2007 ዓ.ም በኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፎር አፍሪካ (ECA) ትልቅ ወርክሾፕ ተካሂዶ ነበር። በዚህ ወርክሾፕ 25 ያህል ጥናታዊ ጽሁፎችም ቀርበው ነበር። በወርክሾፑ መቋጫ ላይ ምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛ ግጭቶች፣ የድህነት መገለጫዎች፣ ድርቅ እና የመሬት መራቆት የሚያጋጥማት መሆኗ ስራዎችን በተበታተነ መልኩ ከምትሰራ በተቀናጀ አሰራር (Integration approach) ብትሄድ ለውጥ ታመጣለች የሚል ግንዛቤ ላይ ተደረሰ። ኬኒያ ታዲያ በምስራቅ አፍሪካ ኔትወርክ አቋቁሙን ኬኒያ የማስተባበሩን ኃላፊነት ወሰደች። እባው ያስን በየሀገራችን ለምን ፒ ኤች ኢ (PHE) አናቋቁምም የሚል ሀሳብ ሲነሳ በወሳኝ መልኩ አስተዋፅኦ ያደረጉት ሰባት ድርጅቶች ነበሩ።

ሰንደቅ፡- ድርጅቶቹን ሊዘረዝሩልን ይችላሉ?

አቶ ነጋሽ፡- በሚገባ! እንደኛ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ ለም ኢትዮጵያ፣ ኮንሶርቲየም ኦፍ ሪፕሮዳክቲቭ ሄልዝ አሶሴሽን (Chorha)፣ ሆርን ኢንቫይሮሜንታል ኔት ወርክና ኢንጀንደር ሄልዝ የተባሉት ድርጅቶች ዋና መስራች በመሆን እንቅስቃሴው ወደተግባር እንዲመጣ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። በዛን ጊዜ የእኔ ሚና ኮሚቴውን እንዳስተባብር ስለመረጡኝ እንደ አስተባባሪ ከእነርሱ ጋር በመሆን አብረን ስራውን ጀምረነዋል። እነዚህ ሰባት ድርጅቶች በገንዘብም ሆነ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ሚናዎችን ተጫውተዋል። ከእነዚህ ሰባት ድርጅቶች በተጨማሪ ደግሞ ፓካርድ ፋውንዴሽን ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል። የፓካርድ ሚናም ቀላል አይደለም። በአጠቃላይ ከአድሆክ ኮሚቴው በተጨማሪ ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ሳይቀሩ፤ አጋር በመሆን የእንቅስቃሴው የበላይ ጠባቂ ሆነዋል። ወደ 51 የሚሆኑ አባል ድርጅቶች አሉት። ትልልቆቹን ኔትወርኮች እንደ ሲ ሲ አር ዲ ኤ (CCRDA) ፓስቶራሊስት ፎረም፣ እንደ ቤን እና የመሳሰሉት ሁሉ የዚህ ሂደት አጋሮች በመሆን ለስኬቱ አስተዋፅኦ አድርገዋል። በአጠቃላይ ይህ ሂደት የሁሉም ጥረት ውጤትና ስኬት መሆኑን መግለፅ እፈልጋለሁ።

ሰንደቅ፡- ስለ ፒ ኤች ኢ (PHE) ፅንሰ ሃሳብ ቢያብራሩልኝ?

አቶ ነጋሽ፡- የፒ.ኤች.ኢ ፅንሰ ሃሳብ እና ትልቁ መነሻ በአገራችንም፣ በምስራቅ አፍሪካም ሆነ በሌላው ዓለም የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መምጣት ነው። ህዝብ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ራሱን ለመመገብና ለመኖር ባለው ፍላጎት ደኖችን ወደ እርሻ ቦታነት በመለወጥ ደኖች ሲወድሙ ያለው የውሃ መጠን እየቀነሰ፣ የእርሻ ቦታዎች እየተሸረሸሩ፣ ወደ ምድረ-በዳነት እየተለወጡ ይገኛሉ። በመሆኑም አገራችንም ሆነ ሌላው ዓለም ውስብስብ ወደሆነ ችግር እየገባ ይገኛሉ። ይህን ውስብስብ ችግር ለመፍታት የልማት አቅጣጫዎች አልነበሩም ማለት አይቻልም። ነበሩ! ነገር ግን አቅጣጫዎቹ የተበታተኑ ነበሩ። ለምሳሌ ጤናን በጤና አቅጣጫ ብቻ፣ ትምህርትንም እንዲሁ በትምህርት መንገድ ብቻ፣ አካባቢያዊ ጉዳይን በአካባቢ ብቻ የማየት እና በዘርፍ የተገደበ አካሄድ (Sectoral Approach) በሚባለው መልኩ ነበር የሚሰሩት። እንግዲህ አገሮች የያዙትን የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ (MDGS) የPASDEP ፕሮግራም በተበታተነ መልኩ ከማስኬድ ይልቅ በተቀናጀ መልኩ ቢተገብሩት ልማት ሊፋጠን ይችላል። የኅብረተሰቡም ጥያቄ ሁሉን አቀፍ በመሆኑ በተቀናጀ አሰራር ምላሽ ለመስጠት ያስችላል የሚል እምነት በመያዝ ነው ይህን የልማት አካሄድ እየተከተልን ያለነው። የልማት አካሄዱ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይሄ ሆኖ ሳለ፣ በንድፈ ሃሳብ ኅብረተሰብን ማሳመን ስለማይቻል ተጨባጭ የሆነ የሙከራና የትግበራ ፕሮግራሞች የግድ አስፈላጊ ናቸው። በመሆኑም ይህ የልማት አቅጣጫ ይሄን መንገድ እንከተል ብቻ አይደለም የሚለው። በተጨባጭ የትግበራ አካባቢዎችን በመለየት የፒ ኤች ኢ ሳይቶች በትግራይ በራያ ላይ፣ ከለም ኢትዮጵያ፣ ሰሜን ሸዋ ሁለት ወረዳዎች በጊዳ ኦ ዞን ምናጉ ወረዳ፣ ኢትዮ ዌት ላንድስ መቱ ወረዳ፣ መልካ ማኅበር በባሌ ዲንሾ ወረዳ፣ ጂብሲዶ ዜጠኝ የጉራጌ ዞን ወረዳዎችን ይህ ሁሉ አባል ድርጅት በተጨባጭ የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ እየተከተሉ ነው። ሲ አር ዲ ኤም በበኩሉ እንደ ኮንሶርቲየም ከፓካርድ ባገኘው ድጋፍ በሰሜን፣ ወላይታ፣ ሀዲያ፣ ከምባታና ሲዳማ ላይ እንደነዚህ አይነት ፕሮጀክቶችን ጀምረዋል።

ሰንደቅ፡- አብዛኛው የልማት አቅጣጫው አገር አቀፍ ነው?

አቶ ነጋሽ፡- አገር አቀፍ ሆኖ ግን ከላይ የጠቀስናቸው ሳይቶች የትግበራ ማሳያ ቦታዎች ናቸው። እነዚህን የትግበራ የሙከራ ስራዎች ኅብረተሰቡ ጠቃሚነታቸውን ከተረዳ በራሱ መንገድ ያስፋፋቸውና እያጠናከራቸው የሚሄድባቸው ማሳያ ናቸው። ስለዚህ ይህ አካሄድ አገር አቀፍ የሆኑ የአቅም ግንባታ ስራዎች፣ አገር አቀፍ የሆኑ የግንኙነት ስራዎች አገር አቀፍ የሆኑ የኔትወርኪንግ አጋርነቶች አገር አቀፍ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎች፣ ይካሄዳሉ። በተጨማሪ ግን እነዚህ የተቀናጀ አካሄድ የሙከራ ሳይቶች ከእነሱ ስኬቶች ለአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ፖሊሲዎች ተፅዕኖ መፍጠር በሚችሉበት መንገድ ማስተማሪያ እንዲሆኑ የማስፋፋት ኃላፊነትም አለብን። ስለዚህ ይህ አካሄድ ይህን ውስብስብ ችግር ለማቃለል ጥሩ አማራጭና ልማትን ሊያፋጥን የሚችል ነው ከሚል እምነት ነው እያካሄድነው ያለነው።

ሰንደቅ፡- ቅድም ስልጠናው ላይ ባቀረቡት ፕሬዘንቴሽን ፒ ኤች ኢ ኮንሶርቲየም ኢትዮጵያ የሦስት ዓመት እድሜ እንዳለው ሲገልፁ ሰምቻለሁ፤ በዚህ ሦስት ዓመት ውስጥ ምን ተሰራ? በተጨባጭ ውጤት አመጣንበት የሚሉት ካለ ቢገልፁልኝ?

አቶ ነጋሽ፡- አዎ በጣም ተጨባጭ የሆኑ ውጤቶች አሉ። አንዱ ኮንሶርቲየሙ ተቋቁሞ ቀጣይነት ኖሮት እዚህ መድረሱ ነው። ለአባል ድርጅቶች የአቅም ግንባታ ስራዎች እንሰራለን። ከእነዚህም ውስጥ ፒ ኤች ኢ በቅንጅት ሲሰራ እንዴት ነው ዲዛይን የሚሆነው? በምንስ መልኩ ነው የፒ ኤች ኢ ስራ ቁጥጥርና ግምገማ የሚካሄድበት? እንዴትስ ለፖሊሲ አውጭዎችና ለሌላው ዓለም በሚመች መልኩ የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራ የሚሰራው? እንዴት ነው ይሄ እንቅስቃሴ በአንዳይን ተደግፎ ሊጠናከር የሚችለው ወዘተ... በሚል ስልጠናዎችን ሰጥቷል።

በተጨማሪም አባል ድርጅቶችን በማሳመን እስካሁን 48 አባል ድርጅቶችን አፍርቷል። ከሁሉም በላይ ግን ባለፉት ሦስት ዓመታት ስንጀምረው መናገሻ አካባቢ የነበረው የፒ ኤች ኢ የተቀናጀ ስራ አሁን በመላው አገሪቱ በሰባት ድርጅቶች ከ30 በላይ ወረዳዎች የተቀናጀ ስራ ለመስራት ችለናል። ይሄ ጅምር አንዳንዱ በፓካርድ ፋውንዴሽን ድጋፍ፣ አንዳንዱ ደግሞ በአይሪሽ ኤይድ፣ በኖሮጂያን ዴቨሎፕመንት፣ በሲዳ እና በተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ነው። ሆኖም አሁን ስልጠና ላይ ያየሻቸው ከእነዚህ ፕሮጀክት ቦታዎች ወጣቱን የሚያስተባብሩ አካላት ናቸው። እነዚህ ወጣቶች በየአካባቢያቸው ያሉ አቻ ቡድኖችን እንዴት ማንቀሳቀስና ማስተባበር እንዳለባቸውና በእንዲህ ዓይነት የተቀናጀ ልማት ወጣቱን እንዴት ማሳተፍ እንደሚችሉ የሚያግዝ ስልጠና በመውሰድ ላይ ይገኛሉ። ይሄ የሚያሳየው የኮንሰርቲየሙን ተጨባጭ ውጤቶች ነው። ሌላው የፈጠርነው አጋርነት ነው። ለምሳሌ ከሌሎች ኮንሶርቲየሞች፣ ከመንግስት አካላት፣ ሌላው ቀርቶ እዚህ አገር ካሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ፓርትነርሽፕ መስርተናል። የተለያዩ ብሮሸሮች፣ ቡክሌቶች እና ሌሎች ሕትመቶችን በማሳተም ኅብረተሰቡ በተቀናጀ የልማት ስራ ላይ ያለውን ግንዛቤ በማስፋት ላይ ነን፡ ነገር ግን አሁን ያለው ውጤት ከተነሳንበት ዓላማ አንፃር ሲታይ እጅግ በጣም ጥቂት ነው። ምክንያቱም የችግሩ ስፋትና ጥልቀት ብዙ በመሆኑ ነው። እርግጥ የተፈጥሮ ሀብታችን መጠበቅ ካለበት፣ ሰውና ተፈጥሮ መታረቅ ካለባቸው፣ የውሃ ሀብታችን ከአደጋ ሊድን ከሆነ ይህ አካሄድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። በርካታ በተቀናጀ አካሄድ መሠራት ያለባቸው ስራዎችም አሉ። በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ያሉ ሐይቆቻችን አደጋ አለባቸው ሊድኑ የሚችሉት በእንዲህ አይነቱ የልማት አቅጣጫ ነው። በአጠቃላይ የችግሩ ስፋትና የእኛ አስተዋፅኦ የሰማይና የምድርን ያህል ርቀት ቢኖረውም፣ ጥረታችን ለለውጥ የራሱ አስተዋፅኦ አለውና እንቀጥላለን።

ሰንደቅ፡- አሁን በተቀናጀ መልክ ስለሚካሄድ የልማት አቅጣጫ አዋጭነት እየተነጋገርን ነው። አሁን ቴክኒካዊ ወደሆነው ነገር እንምጣና፤ ስነ-ህዝብ፣ ጤናና አካባቢ ምንና ምን ናቸው? እነዚህ ተቀናጅቶ ከመሄድ የሚገኘው ትሩፋትስ ምን ይመስላል?

አቶ ነጋሽ፡- ጥሩ ጥያቄ ነው በእውነቱ፣ በእኔ አገላለፅ የዓለም የልማት አቅጣጫ ጠቃሚነቱ ለህዝብ ነው። ተጠቃሚውም የሂደቱ ባለቤትም መሆን ያለበት ህዝቡ ነው። ነገር ግን ህዝቡ ከተፈጥሮ እንዳይጠቀምና የሂደቱም ባለቤት እንዳይሆን የተለያዩ መሰናክሎች እየተፈጠሩ ነው ያሉት፤ በአንድ በኩል እልሚ ዜጋ እንዳይሆን የሚከለክሉ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ህዝብ የሂደቱ ባለቤት የሚሆነው አልሚ ሲሆን ነው። አልሚ የሚሆነው ደግሞ ተምሮና አቅም ፈጥሮ እውቀትን በማዳበር ተፈጥሮን መጠቀም ሲችል ነው። ይህ እንዳይሆን የከለከለው በጣም የተጠናከረ ድህነት መኖሩ የድህነቱ መገለጫ ደግሞ የሚበላው አጥቶ እስከመራቆትና ተፈጥሮ ላይ ብቻ ጥገኛ እስከመሆንና ተፈጥሮን በማራቆት ብቻ የሚኖርበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል። ይባስ ብሎ የህዝቡ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ሌላው ችግር ነው። እንደምታውቂው በአሁኑ ወቅት የዓለም ህዝብ ሰባት ቢሊዮን ደርሷል። በ2050 ዓ.ም አንዳንዶቹ ስምንት ቢሊዮን ልንደርስ እንችላለን ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ በአማካኝ ዘጠኝ ቢሊዮን ልንሆን እንችላለን ይላሉ። ሌሎቹ በበኩላቸው አሁን ያለው የወሊድ ሁኔታ ከቀጠለ 11 ቢሊዮን ልንደርስ እንችላለን እያሉ ነው። ወደ ኢትዮጵያ መለስ ስትይ፣ በ2020 የኢትዮጵያ ህዝብ 130 ሚሊዮን ሊደርስ ይችላል። በ2050 የኢትዮጵያ ህዝብ 170 ሚሊዮን አካባቢ ሊደርስ እንደሚችል እየተገመተ ነው። አስቢው፣ መሬት እየጠበበች ህዝቡ እየጨመረ ነው። ተፈጥሮም በአየር ሚዛን መዛባትና በሌሎች አደጋዎች እየተጎዳች ነው። ስለዚህ ለመኖር ያለውም እድል እየጠበበ ነው ያለው። ስለዚህ ህዝቡ ተምሮ አቅም ፈጥሮና ዓለሙም ሆኖ በዘላቂነትና አቅም በመፍጠር ችሎታ ካልዳበረ አደጋው በጣም ሰፊ ነው። ስለዚህ ስነ-ህዝብ፣ ጤናና አካባቢ የማይነጣጠሉ ቁርኝታቸውም እጅግ የጠበቀ ነው። እነዚህን ሦስት ነገሮች በማቀናጀት ህዝብና ተፈጥሮን ማስታረቅ የወቅቱ ዓለም አቀፍ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ሦስቱን ነገሮች ከማቀናጀት የሚገኘውም ጥቅም ህዝብና ተፈጥሮን በማስታረቅ ሊመጣ ካለውና እየመጣ ካለው አስጊ አደጋ መላቀቅ ነው። ጤነኛ ተፈጥሮ ሲኖር ነው ጤናማ ኅብረተሰብ የሚኖረው። ይህ ሁሉ በተቀናጀ የልማት አቅጣጫ ነው ሊሳካ የሚችለው።

> ሌላው ከጅማ አልፈሽ ጅማ
> ከተማውም ሳይቀር ያሉ ወንዞችና
> ገባሮቻቸው ይዘውት የሚመጡት
> አፈር አመቱን ሙሉ የማይቋረጥ
> ነው። እነዚህ ችግሮች ግድቡ ሲሰራ
> እስከ 70 ዓመት ይገባል ተብሎ
> ከተገመተው ደለል በላይ በመግባቱ
> የተፈጠሩ ናቸው። ለዚህ ችግር
> አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች
> ውስጥ አንደኛ የአካባቢው ህዝብ
> በድህነት ውስጥ ያለ በመሆኑ
> መከላከል የሚችሉ ዛፎች
> በመቆረጣቸው፣ በደን የተሸፈኑ
> ቦታዎች ወደ እርሻነት
> በመለወጣቸው፣ ሌላው ቀርቶ በቡና
> ዛፍ የተሸፈኑትን ለእህል እርሻነት
> እየተለወጡ በመምጣታቸው
> በርካታና ሰፊ መሬት ለአፈር
> መሸርሸር ምቹ ሆነው ተገኝተዋል።

ሰንደቅ፡- በቅርቡ ግልገል ጊቤ አንድን በተመለከተ አንድ መረጃ ወጥቶ ነበር። ይሄውም ግልገል ጊቤ አንድ ሲሰራ ለ70 ዓመታት አገልግሎት እንዲሰጥ ቢሆንም፣ አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ከ24 እስከ 30 ዓመት ብቻ እንደሚያገለግል ከጅማ ዩኒቨርሲቲ የወጣ አንድ ጥናት ይፋ አድርጓል። እናንተም ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር አንድ ወርክሾፕ ማካሄዳችሁን ሰምቻለሁ፤ ጉዳዩን ሰፋ አድርገው ቢያብራሩልኝ?

አቶ ነጋሽ፡- እኛ መጀመሪያ ያደረግነው ጅማ ዩኒቨርስቲዎች ምን ጥናት እንዳላቸው፣ ጥናቱስ አብሮ ለመስራት ያስችለናል ወይ? የሚለውን ጉዳይ ተመለከትን፣ ጥናቱስ እስከ ወርክሾፕ የሚደርስ ነው ወይ? መረጃስ አለው? በሚል ከዩኒቨርስቲው ጋር ተወያየን፤ «አዎ መረጃ አለን ግልገል ግቤ አንድ ዋናውና ገባሩ (Upper Water Shale) ላይ ጥናት አለን፤ ስለዚህ አጋዥ የሆነ ደግሞ የታችኛው (Lower) ላይም አለን» አሉ። እኛም አየነው። ጠቃሚ ማቴሪያል ሆኖ አገኘነው። ይህን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን (EPPCO) አወያየን ግልገል ጊቤ ስትራቴጂያዊ ነው ቀጣይነቱም አደጋ ላይ ነው። ኅብረተሰቡን፣ ክልሎችን፣ የሚመለከታቸውንና ባለድርሻ አካላትን ማሳመን ይጠይቃል። ስለዚህ እንዴት ነው አብረን እንቅስቃሴ ማድረግ የምንችለው ብለን አቶ ምህረት ደበበን ስንጠይቃቸው፣ ጉዳዩ በጣም የሚፈለግ ነው። ይሄ ትልቁ ክፍተታችን ነው በማለት አመኑበት። መመሪያም አወረዱ። ውሃና ኢነርጂንም አሳመንን። ይሄ ጉዳይ በጣም ንገብጋቢ እና የሚጠቅመንም ነው ተባለ። በዚህ ሁኔታ በውሃና ኢነርጂ አስተባባሪነት የመንግስት አካላት ደብዳቤ አወጡ። እኛ በበኩላችን በጥናቱ ከመግፋት በተጨማሪ ሄንሪሽ ቦል ፋውንዴሽን ፋውንዴሽንን ስፖንሰር እንዲያደርጉን በማሳመን፤ ለዚህ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የተለያዩ አካላትን በመጥራት የሦስት ቀን ወርክሾፕ ከነጉብኝቱ አካሄድን ግልገል ጊቤም ተጎበኘ። ይህ ጥናት ያሳየው ሰባ ዓመት የነበረው በ24 ዓመት አገልግሎት መቆሙን ብቻ አይደለም፣ ከ70 ዓመት በላይ ቀጣይነት እንዲኖረው እንጂ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንም በቀጣይ ስትራቴጂው ውስጥ እንዲያካትተውም ጭምር እንጂ! ክልሎችንም በተለይ ኦሮሚያንና ደቡብን በማሳመን ለራሳቸውም ውጤት የሆነ ስራ እንደሆነ ማሳመን፤ ዩኒቨርስቲዎች ቀጣይና ኅብረተሰብ ተኮር የሆኑ ጥናቶች ማድረጋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ የሚመለከተው ግብርና ለአፕሮካችመንቱ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ እና ለዘላቂ የመሬት ማኔጅመንት (Sustainable Land Management (SLM)) የሚለው ፕሮጀክታቸው እዛ አካባቢ ስራ እንዲጀምር በመጀመሪያ 10 ሺህ ከዚያም 40 ሺህ ሔክታር ለማልማት እቅድ ይዘዋል። የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኅብረተሰቡን ንቃት ሄደው በመጎብኘት እንዴት አቅማቸውን ማጠናከር እንደሚችሉ በሌላ በኩል ሲቪል ማኅበረሰብ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመደገፍ በግልገል ጊቤ ብቻ ሳይሆን ኮካ ዝዋይም ሆነ በአዋሽ ስራ ጀምረዋል። ይህ ጅምር በጥሩና በተጠናከረ ሁኔታ ከቀጠለ 70 ዓመት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ጥቅም ላይ የማዋል ስራ እድል እንዳለ ሁኔታዎች ያመለክታሉ። የግልገል ጊቤን እድሜ በማራዘም የበለጠ ግልጋሎት የሚሰጥበት ፓርትነርሽፕ ነው። ይህ አጋርነት ብሔራዊ ግብረኃይል ተቋቁሞለታል። ይህ ግብረ ኃይል በውሃና ኢነርጂ የሚመራ ሲሆን፤ ግብርና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሞፍኤድ፣ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን፣ ትምህርት ሚኒስቴር ዩኒቨርስቲዎችን በማስተባበር፣ ደቡብና ኦሮሚያ የተካተቱበትና የእኛም ኮንሶርትየም አባል የሆነበት ግብረኃይል እንዲቋቋም ተወስኗል።

ሰንደቅ፡- የግብረ ኃይሉቹ ስራ በዋናነት ምንድን ነው?

አቶ ነጋሽ፡- የግብረ ኃይሉ መቋቋም እንደግልገል ጊቤ ያሉትንም ሆነ በስምጥ ሸለቆ አካባቢ ያሉ የኃይቆቻችን ችግሮች በአንድ ሚኒስቴር ብቻ የሚፈቱ ባለመሆናቸው ተቀናጅተን ስራችንን አስተባብረን በተቀናጀ መንገድ መሄድ ያስፈልጋል። ስለዚህ ግብረኃይሉ ለዚህ ስራ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሚኒስትሮችና የልማት ኢጀንሲዎች አንድ ላይ በፖሊሲ ዙሪያና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ተቀናጅተው የሚፈቱበት ሁኔታ ለማመቻቸት ነው ወቅቱ የሚጠይቀው አካሄድም ይሄው ነው። ይህንን ደግሞ ግብርና ሚኒስቴርም፣ አካባቢ ጥበቃም፣ ውሃና ኢነርጂም፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንም በጣም ይፈልጉታል። ክልሎችም እንዲሁ ከዚህ አንፃር ነው ይሄ ግብረኃይል (task force) እንዲቋቋም የተወሰነው።

ሰንደቅ፡- ግልገል ጊቤ አንድ አሁን ከሰባ ዓመት ከ24 እስከ 30 ዓመት ብቻ አገልግሎት እንዲወርድ ያደረገው የደለል ከአቅም በላይ ወደ ግድቡ መግባት እንደሆነ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት፤ እናንተ ጥናቱን ስትመለከቱና ሄዳችሁ ስትጎበኙ ለዚህ ችግር መፈጠር በዋናነት የሚጠቀሱ አካባቢያዊ ችግሮች ምንድን ናቸው ይላሉ?

አቶ ነጋሽ፡- ጥናቱ እንደሚያሳየው በመጀመሪያ ግድቡ ሲሰራ ግድቡ ያለበት ቀጠና ደግሞ ከግድቡ ጥግ ያለ ከእንስሳትም፣ ከህዝብም ሆነ ከእርሻ ንክኪ ንፁህ በማድረግ ወደ ግድቡ የሚገባው ውሃ በተቻለ መጠን አፈር እንዲቀንስ የሚያስችል እቅድ ነበራቸው። ይህ እቅድ ግድቡ እስከሚሰራ ድረስ በጥሩ ሁኔታ ሄዷል። ግድቡ ከተሰራ በኋላ ግን አካባቢውን በደንና በሣር በመሸፈን ከእንስሳት፣ ከእርሻና ከህዝብ ንክኪ ንፁህ አድርጉ የመቀጠሉ ስራ ባለቤት ስላጣ፤ ኅብረተሰቡ አስቀድሞ ከዚያ አካባቢ እንዲወጣ ተደርጉ የነበረ ቢሆንም፣ ተመልሶ ወደ አካባቢው በመምጣት የእርሻ ቦታ አደረገው። በዚህ ምክንያት አፈር በብዛት መግባት ጀመረ። ሌላው ከጅማ አልፈሽ ጅማ ከተማውም ሳይቀር ያሉ ወንዞችና ገባሮቻቸው ይዘውት የሚመጡት አፈር አመቱን ሙሉ የማይቋረጥ ነው። እነዚህ ችግሮች ግድቡ ሲሰራ እስከ 70 ዓመት ይገባል ተብሎ ከተገመተው ደለል በላይ በመግባቱ የተፈጠሩ ናቸው። ለዚህ ችግር አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ አንደኛ የአካባቢው ህዝብ በድህነት ውስጥ ያለ በመሆኑ መከላከል የሚችሉ ዛፎች በመቆረጣቸው፣ በደን የተሸፈኑ ቦታዎች ወደ እርሻነት በመለወጣቸው፣ ሌላው ቀርቶ በቡና ዛፍ የተሸፈኑትን ለእህል እርሻነት እየተለወጡ በመምጣታቸው በርካታና ሰፊ መሬት ለአፈር መሸርሸር ምቹ ሆነው ተገኝተዋል።

ሌላው ለዚህ ችግር አስተዋፅኦ የሚያደርገው የልማት አቅጣጫችንም ነው። ይህ ማለት የተለያዩ ወረዳዎች፣ ዞኖች፣ ክልሎች እና በፌደራል ደረጃ የሚሰሩትም አንዱ ሲሰራ ሌላው ላይ ጉዳት በማያመጣ መልኩ እንዲሆን ከእቅድ ጀምሮ ተቀናጅቶ የመስራት ሁኔታ አልነበረም። የመናበብ

ወደ ገፅ 20 ዞሯል

ሥነ-ሕዝብንና...

ችግርም ነበር፡፡ ግብርናም ግብርናውን ብቻ ነው የሚያስበው፤ ሌላውም እንዲሁ፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የአፈር መሸርሸሩና ወደ ግድቡ ከአቅም በላይ ለመግባቱ ምክንያት ሆኗል፡፡ ኅብረተሰቡስ ቢሆን ስለ ግድቡ ምን ያህል ግንዛቤ አለው? አሁን እያደረገ ያለው ስራ የበለጠ ራሱን እንደሚጎዳውስ ያውቃል ወይ? የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት፡፡ አሁን ወረዳው ከመርኀዎቹ በኋላ እያደረጋቸው ያሉ እንቅስቃሴዎች አስቀድመው አልተሰሩም ነበር፡፡ ቀደም ሲል ቢሰሩ አደጋውም አይጋረጥም ነበር፡፡ አሁን ግን መንግስትም ክልሎችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላትም በትኩረት እጃቸውን በጉዳዩ እያስገቡ ነው ኤፒኮም ግድብ መስራት ብቻ ሳይሆን ቀጣይነቱም ላይ በስትራቴጂው አካቶ እየሰራ ስለሆነ የመፍትሔ አቅጣጫ ይዟል ማለት ይቻላል፡፡

ሰንደቅ፡- ስለዚህ በዚህ ወርክሾፕ ላይ የእናንተ ዋናው ሚና የአድቮኬሲ ስራ ነው ማለት ይቻላል?

አቶ ነጋሽ፡- የእኛ ዋናው ስራ መረጃን አደራጅቶ መንግስት የጎደለውን አካባቢ ክፍተት እንዲሞላ ማገዝ ነው፡፡ የእኛ ዋናው ስራ ክፍተት ስናይ ማመላከት ነው፡፡ የእኛ ስራ መንግስትን ተክቶ መስራት ሳይሆን በያዘው የልማት አቅጣጫ ላይ ድጋፍ በመስጠት የልማት አቅጣጫውን እንዲያጠናክር ማገዝ ነው፡፡ ይሄና ይሄ ነው የልማት አቅጣጫችን፡፡

ሰንደቅ፡- በተለይም በእኛ አገር ቀደም ባሉት ዓመታት የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ብዙ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም፤ እቅዶችና ስትራቴጂዎች ሲነደፉም ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር የተቃኙ እንዳልነበሩ የሚናገሩ ምሁራን አሉ፤ አሁን አሁን ጉዳዩ ትኩረት ቢያገኝም፡፡ እናንተ የፒ ኤች ኢን ኀሳብ ይዛችሁ ስትነሱና ወደ ስራውም ስትገቡ የገጠሟችሁ ፈተናዎች የሉም?

አቶ ነጋሽ፡- በእኔ እምነት እኛ ችግሩን ለይተን የኮንሶርቲየሙ ስራ ያስፈልጋል ካልንበት ጀምሮ ከመንግስት ጥሩ ትብብር አግኝተናል፡፡ ለምሳሌ ለሕጋዊነታችን ፍትህ ሚኒስቴር ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው ለእኛ ደብዳቤ የፃፈልን አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡ ባለስልጣኑ መጀመሪያውኑ እድሆ ኮሚቴ ውስጥ ሆኖ የዚህን ሂደት አስፈላጊነት ያምን ስለነበረ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አልፎም ካስተዋልሽው እኛ ስራ በጀመርንበት ጊዜ መንግስት በተጠናከረ መልኩ ዛፍ እንትከል የሚል ሰፊ ዘመቻ ውስጥ የገባበት ወቅት ነበር፡፡ ሌሎች እንቅስቃሴዎችም ነበሩ፡፡ አሁንም በቅርቡ ደግሞ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (GTP) በጣም አጋዥ የሆኑ ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ ዜሮ የካርበን ልቀት በ2025 የሚሉትን አቋሞች ጨምሮ እኛ አካባቢያዊ ስራዎችን ለመስራት ፖሊሲዎቹም አጋጣሚዎቹም ሰፊ እንደሆኑ ጠቋሚ ናቸው፡፡ ቻሌንጆቻችሁ ምንድናቸው ላልሽው፤ አፈፃፀም ላይ ነው ለጋሾችም፣ የመንግስት አካላትም አካሄዳቸው የዘርፍ አካሄድ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ሴክተሮች ላይ በጣም ግልፅ በሆነ መልኩ አስቀምጧል፡፡ ስራው እንዴት በተቀናጀ መልኩ ይሰራ የሚለውን አይመልስም፡፡ ይሄ ክፍተት አንዱ ፈተናችን ነው፡፡

የሴክተር አካሄድም በቀላሉ የምትለውጭው አይደለም፡፡ በጣም የተዛባ አስተሳሰብ ያለበት ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የህዝቡ ቁጥርና ድህነቱ በተፈጥሮ ላይ የሚፈጥረው ጫና እና የመንግስት አስተዋፅኦ ለብቻው መፍትሄ የሚሰጠው አይደለም፡፡ ከሌሎች አካላት ከፍተኛ የሆነ ቅንጅት ፈጥሮ ፈጣን የሆነ እርምጃ የሚፈልግ ነው፡፡ አፈፃፀም ላይ የሚፈለገው ፍጥነት አለ ወይ የሚለው የራሱ ገደብ አለው፡፡ ሌላው ቻሌንጅ መንግስት በተጠናከረ ሁኔታ ወደዚህ ስራ እንዲገባ ድጋፍ ያስፈልገዋል፡፡ እኛ ሲቪል ማኅበራት ምን ያህል ነን ግልፅነት ይዘንና አቅም ፈጥረን የመንግስትን ክፍተቶች ለይተን በተጨባጭ ልናግዘው የምንችለው የሚለው ራሱ ፈተና ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር በአየር ንብረት ለውጥ ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ቦታ አላት፡፡ ሆኖም የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአመራር ቦታና በተጨባጭ በተግባር የሚሰራው ስራ ከፍተኛ ርቀት ያለው በመሆኑ ይህን ክፍተት ለማጥበብ ከፍተኛ ስራ ይጠይቀናል፡፡ ይሄም ፈተናችን ነው፡፡ ለእነዚህ ፈተናዎች ትኩረት ሰጥተን በመቀናጀትና በመናበብ ገንቢ ወደሆነ አጋርነትና ትብብር ከመጣን ፈተናዎቹ ልናልፋቸው የማንችላቸው አይደሉም፡፡ እንደኮንሰርቲየማችን የእኛ አቅም በጥናት ተደግፎ መረጃን መሠረት ያደረገ ሆኖ፤ አሁን የጀመራቸውን ጥሩ ጅምሮች እና ውጤታማ ስራዎች ሌላው እንዲማርባቸው ለማድረግ ብንሞክር ለልማት የተሻለ አስተዋፅኦ ልናደርግ እንደምንችል እናምናለን፡፡

ሰንደቅ፡- በአሁኑ ሰዓት እጅግ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ለባለሃብቶች እየተሰጡ ይገኛሉ፤ በዚህ ምክንያት በርካታ የሐይቅ ውሃዎች እየተወሰዱ በሐይቆች ላይ አደጋ እያንዣበበ እንደሆነ እየተነገረ ነው፤ የደኖች ጉዳይም እንዲሁ፤ እናንተ ይህን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል የማመላከት ስራ ለመስራት አላሰባችሁም?

አቶ ነጋሽ፡- በእርግጥ መንግስት የተጠናከረ ልማት ለማፋጠን በቀጣይ አምስት ዓመት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ ሰፋፊ መሬቶችን በመለየት የውጭ ባለሀብቶች መጥተው እንዲያለሟቸው እያደረገ ነው፡፡ ዓላማው የምንደግፈው ነው፡፡ ልማትም መፋጠን አለበት፡፡ ስኬታማ እንዲሆንም አስተዋፅኦ ማድረግ ይገባናል፡፡ ይሄ ትልቁ እምነታችን ነው፡፡ ሲፈፀሙ ግን በአንድ በኩል በተለይ ደን በማስወገድ የሚደረጉ የእርሻ እንቅስቃሴዎች ደኑ ለኢኮ ሲስተሙ ያለው አስተዋፅኦ፤ የደኑ ጥቅምና ወደ እርሻ ከመለወጥ የሚገኘው ጥቅም ተወዳድሮ በጥናት ነው ወይ የሚፈፀመው የሚለው የሚመለከተን ነው፡፡ ሁለተኛ ሀገራችን የዌትላንድ ፖሊሲ የላትም፡፡ ዌትላንዶች (ውሃ አዘል መሬቶች) ደግሞ የኢኮ ሲስተሙ ቁልፍ ቦታዎች ናቸው፡፡ ዌትላንዶች ለእርሻ ምቹ ናቸው፡፡ ዌትላንዶች ለቤት እንስሳም ለውሃም ሆነ ለተለያዩ ነገሮች ምቹ የሆኑ ጠቃሚ ቦታዎች ናቸው፡፡ በሀገራችን ከ2 በመቶ በላይ ረግረጋማና ውሃ አዘል ቦታዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ግን በከፍተኛ አደጋ ላይ ያሉት እነሱ ናቸው፡፡ መንግስት በሚሰጣቸው የእርሻ ቦታዎች ልክ እንደ ደኑ በደንብ አይቶና አነፃፅሮ እርምጃ መውሰድ አለበት እንዳልነው ዌትላንዶችም ተጠንተው ጥቅምና ጉዳታቸው ከእርሻ ከሚመጣው ጥቅም ጋር ተነፃፅሮ እርምጃ መወሰድ ይገባዋል፡፡ ይህ በጥናት የተደገፈ ነው ወይ የሚለው ይመለከተናል፡፡ ታዲያ ለሚመለከተን ጉዳይ ሁሉ በመጮህና በመቃወም ሳይሆን በጋራ ጉዳዮችን በማጥናትና በመስራት እነዚህን አስጊ ቦታዎች ከአደጋ በሚያድን ሁኔታ አጠቃላይ ኢኮ-ሲስተሙን በማያዛባ ሁኔታ እንዲፈፀም ስለምንፈልግ ከመንግስት ጋር አብሮ የመስራት የመወያየትና ችግሮች ካሉም በውይይት የሚፈቱበት መንገድ የመፍጠርና በዚህ ዙሪያ የመስራት ኀሳብ አለን፡፡

ሰንደቅ፡- በብዛት እንደምናየው በርካታ ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ስራዎችን የሚሰሩ ድርጅቶች ይመሰረታሉ፡፡ በተለይ ፋይናንስን በተመለከተ በለጋሾች ላይ ጥገኛ ሆነው ስለሚመሰረቱ ለጋሾች ባሻቸው ጊዜ መለገስ ሲያቆሙ እነዛ ጠቃሚ ድርጅቶችና ስራዎች አብረው ይቆማሉ፡፡ የእናንተ ኮንሰርቲየምም በለጋሾች ድጋፍ ላይ የተመሠረተ ነገር ግን እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ለጋሾች እርዳታ ቢያቆሙ የኮንሰርቲየሙ ህልውና ቀጣይ የሚሆንበት የገቢ ማስገኛ ሜካኒዝም አላችሁ ወይስ እንደተለመደው ስራችሁ ይቆማል?

አቶ ነጋሽ፡- እውነት ለመናገር ጥሩ ጥያቄ ነው መነሳት ያለበትና ወቅታዊም ነው፡፡ ጥሩ የልማት አቅጣጫዎች ሐቀኛ የሆነው የልማት ተጠቃሚ እውን ካላደረጋቸው የትም ሊደርሱ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ለጋሾች ሲፈልጉ ይሰጣሉ ሳይፈልጉ ያቆማሉ፡፡ ስለዚህ እንደ ፒ ኤች ኢ እምነት አቅጣጫ መሆን ያለበት እውነተኛ አካሄድ ከተከተለ ኅብረተሰቡን የጉዳዩ ባለቤት ማድረግና ማሳተፍ መቻል አለብን፡፡ ሁለተኛ እውነተኛ ኅብረተሰቡ ካመነበትና ከተቀበለው በራሱ መንገድ ሊያስኬደው የሚችል የልማት አቅጣጫ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከተፈጠረ ደግሞ መንግስትም ሊደግፈው የሚችለው ነው፡፡ እስካሁን አንዳንድ ጅምሮች አሉ፡፡ ከመንግስት ለመያዶች መስጠት ተጀምሯል፡፡ ይሄ አካሄድ መንግስት ካመነበት ነገ ከያዘው በጀትም ማስፈፀሚያ ለመስጠት የሚያንገራግር አይመስለኝም፡፡ እኛ እዛ ደረጃ ለመድረስ ግን በርካታ የቤት ስራዎችን ማከናወን አለብን፡፡ ይኼ መንገድ ምን ያህል አዋጪ ነው? ምን ያህል ነው ኅብረተሰቡ እውን ያደረገው? ምን ያህልስ ችግሩን ፈቶለታል? እንዴትስ ኅብረተሰቡ በአንድ በኩል ያገኘውን ድጋፍ በቀጣይነት የሚያስኬደው የሚለውን ሂደት በተግባር የማሳየት አቅም መፍጠር አለብን፡፡ ይህን እስካደረግን ድረስ በለጋሾች እርዳታ ማቆም ስራችን ይገታል የሚል እምነት የለኝም፡፡

ሰንደቅ፡- እስካሁን ባነሳነው ላይ ተጨማሪና ከኮንሰርቲየሙ አንፃር መነሳት ያለበት ጉዳይ ካለ ይጨምሩና እንሰነባበት?

አቶ ነጋሽ፡- በጣም ጥሩ! ፒ ኤች ኢ ኢትዮጵያ አዲስ ጅምር ነው፡፡ የቅንጅት ስራ በደንብ ካወቅነውና ከተገነዘብነው በአፈፃፀም እንደ መያድም እንደ መንግስትም ጥሩ ግንዛቤ ይዘን ተግባራዊ ልናደርገው ብንችል ውጤቱ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ አንደኛ የፕሮግራም እና የአፈፃፀም ሲነርጅን ይፈጥርልናል፡፡ እሴትን የሚጨምሩ ውጤቶችን ይጨምርልናል፤ ብቃትንም እንዲሁ ይጨምርልናል፡፡ አሁን ለተያዘው የMDG የGTP እና የPASDEP ፈጣን እንቅስቃሴን ለማድረግ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ይህን አካሄድ የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ ለጋሾችም ጭምር በመከተል እሴትን ከመጨመር ውጭ የሚቀንሱት አንድም ነገር እንደሌለና ለኪሳራ እንደማይዳርጉ መግለፅ እወዳለሁ፡፡ ስለሆነም ይህን አካሄድ እውን ቢያደርጉት የአገራችንን ልማት ያፋጥናል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ አመሰግናለሁ፡፡